# UW Medicine

**የታካሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች**
**የጽ/ቤት ፖሊሲዎችና የአሰራር ደንቦች**

**ፖሊሲ/የአሰራር ሂደት ስም** **የ UWMC እና HMC የሂሳብ ማስከፈያና ዕዳ ማሰባሰቢያ ፖሊሲ**

**ዓላማ፥**

የ University of Washington Medical Center (UWMC) እና የ Harborview Medical Center (HMC) የሕብረት ተልዕኮ፣ የሕክምና እውቀትን በማዳበር፣ ባካባቢ ለሚገኘው ሕዝብ የላቀ የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና እና የስፔሻልቲ እንክብካቤ በማቅረብ፣ እንዲሁም የነገዎቹን ሐኪሞች፣ ሳይንቲስቶችና ሌሎች የጤና ባለሞያዎችን በማዘጋጀት፣ የሕዝቡን ጤና ማሻሻል ነው። ይህንን ተልዕኮ ከግቡ ለማድረስ፣ የሕክምና ማዕከሎቹ የሚከተሉትን የሚፈጽም የዕዳ ስብሰባ ፖሊሲ ያስፈልጋቸዋል፥

A. ለተሰጡት አገልግሎቶች በሰዓቱ እንዲከፈሉ የሚያበረታታ።
B. እያንዳንዱ ግለሰብ ያለውን የፋይናንስ ሁኔታ በግምት ውስጥ የሚያስገባ።
C. ታካሚዎች የክፍያ ግዴታቸውን እንዲውጡ የተለያዩና በቂ አማራጮችን ማቅረብ።

**ፖሊሲ፥**

<u>የመድን ዋስትና የቢል አደራረግ፥</u>
የ UWMC እና HMC የታካሚ ፋይናንስ አገልግሎቶች (Patient Financial Services)፣ የስቴት፣ ፌደራል እና ሌሎች የንግድ የመድን ዋስትና ሰጪዎችን እንዲከፍሉ ይጠይቃሉ። ከመድን ዋስትና አቅራቢዎች ጋራ፣ ክፍያው እንዳይከፈል ውድቅ ለሆነበት ይግባኝም ጨምሮ፣ ለሚኖሩት ጉዳዮች ሁሉ መፍትሔ እስከምናገኝ ድረስ ታካሚው ዕዳውን እንዲከፍል በኃላፊነት ተጠያቂ አናደርገውም። በተቻለን መጠን፣ ማመልከቻው ወደ ግል ከፋይነት ከመቀየሩ በፊት፣ ከመድን ዋስትናው ክፍያን ለማግኘት እንደ የታካሚው ጠበቃ ሆነን እንከራከራለን።

- በግል የሚከፈሉ ሒሳቦች፣ ሌሎች ስምምነቶች ከተደረጉ እንጂ፣ የመጀመሪያውን የሂሳብ ክፍያ መግለጫ ካገኙ ጀምሮ በ 30 ቀኖች ውስጥ መከፈል አለባቸው።
- የመድን ዋስትና ከከፈለ በኋላ በግል የሚከፈሉ ሒሳቦች፣ የመጀመሪያው ክፍያ መግለጫ ከደረስዎ በኋላ በ 30 ቀኖች ውስጥ መከፈል ይኖርባቸዋል።
- UWMC እና HMC፣ የክፍያ መግለጫውን በ 120 ቀናት ጊዜ ውስጥ በየ30 ቀን ይልካሉ።
- በዚህ ጊዜው ውስጥ፣ ታካሚዎች ክፍያን ሙሉ በሙ ለመክፈል ወይም የሚከተሉትን የሚያጠቃልል የፋይናንስ ድርድር ላይ ለመድረስ እድል አላቸው፥
  - የክፍያ እቅድ
  - የፋይናንስ እርዳታ (የበጎ አድራጊዎች)
  - ስለ ሒሳቡ መከራከር
  - ሌላ ከፋይ ወይም የመድን ዋስትና ሒሳቡን መክፈል እንዲችል ተጨማሪ መረጃ ማቅረብ

- የሂሳብ ስብሰባ እርምጃ ከማስወሰዳችን በፊት፣ የእንክብካቤ ጥራትና የቢል አደራረግ ትክክለኝነት ጉዳዮች በተቻለ መጠን በቶሎ መፍትሔ ማግኘት ይኖርባቸዋል።
- ክፍያን ለማግኘት ወይም የፋይናንስ ድርድር ላይ ለመድረስ ወደ ውጭ ስልክ መደወል።
- አራተኛው የክፍያ መግለጫ"የመጨረሻው ማስታወቂያ" ሲሆን፣ በሚቀጥሉት 30 ቀኖች ውስጥ ክፍያ ካልተደረገ ወይም ድርድር ላይ ካልተደረሰ፣ የዕዳ ሒሳባቸው ወደ የውጭ ክፍያ ሰብሳቢ ወኪል እንደሚተላለፍ ለዋሱ የሚያሳውቅ ነው።
- መልስ ሳይሰጡ መቅረት ወይም ክፍያውን ሙሉ በሙሉ አለመክፈል፣ ሒሳቡ ወደ ሰብሳቢ ወኪል እንዲተላለፍ ሊያስደርግ ይችላል ።
- የፋይናንስ ችግር እንዳለባቸው የሚያሳውቁ ሁሉም ታካሚዎች፣ የፋይናንስ እርዳታና/ወይም ምናልባትም የ Medicaid ሽፋን ማጣሪያ ይደረግላቸዋል። የፋይናንስን እርዳታ በማንኛውም ግዜ ላይ ሊፈቀድ ይችላል፣ ይህም ሒሳቡ ወደ ሰብሳቢ ከተላለፈ በኋላም ጭምር ሊሆን ይችላል፣ ቢሆንም ሕጋዊ ፍርድ ከመበየኑ በፊት ተጠይቆ መሆን ይኖርበታል።

<u>ታካሚዎች ቀሪውን ዕዳቸውን ለመክፈል የሚችሉባቸው አማራጮች፥</u>
UWMC እና HMC ጥሬ ገንዘብ፣ ቼክ ወይም ክሬዲት ካርድ ይቀበላሉ። የክሬዲት ካርድ ክፍያዎችን በስልክ ወይም በኢንተርኔት በኩል ባሉ የሒሳብ መክፈያ አማራጮች እንቀበላለን። የታካሚው የክፍያ ድርሻ ከሕክምና ከወጣ በኋላ የመጀመሪያው ቢል እንደ ደረሰው መከፈል ይኖርበታል፣

የመክፈያ መንገድ ስምምነቶች ካሉ ወይም ለፋይናንስ እርዳታ ማመልከቻ ገብቶ ከነበረ በስተቀር።

<u>የክፍያ እቅዶች፥</u>
የክፍያ መንገድ ስምምነቶች የሚመሰረቱት ታካሚው ለታካሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (Patient Financial Services Department) ጥያቄ ሲያቀርብ ነው። ለወትሮው፣ ይህ እስከ 12 ወራት ድረስ እኩል ክፍያ የሚከፈልበትን ጊዜ የሚፈቅድ ይሆናል ወይም ፈቃድ የተሰጣቸው ሁኔታዎች ተፈጻሚ ከሆኑ ደግሞ እስከ 24 ወራት ድረስ ሊሆን ይችላል።

<u>እውነተኛ በገዛ ራስ ክፍያ (የመድን ዋስትና ከሌለ) ቅናሽ፥</u>
የሕክምና አገልግሎታቸው አስፈላጊ ለሆነ በእውነተኛ በግል ክፍያ ለሚያደርጉ(የሕክምና ዋስትና ለሌላቸው) ለተቋሙ ክፍያ የቀረቡ ሁለት ዓይነት ቅናሾች አሉ። ቅናሹ በታካሚዎች የፋይናንስ አገልግሎቶች ተግባራዊ ስለሚደረግ የታካሚው የሒሳብ መግለጫ ላይ ማስተካከያ ሆኖ ይታያል። ቅናሹ የሚያገለግለው ሕመምተኛው ምንም አይነት የሕመምተኛ ዋስትና ከሌለው እና የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ካልሆነ ነው።
- UWMC እና HMC የሕመምተኛ ዋስትና የሌላቸው ሕመምተኞች በድንገተኛ ክፍል ውስጥ ሲታዩ 30% (ሰላሳ በመቶ)ቅናሽ ይደረግላቸዋል
- UWMC ዋስትና የሌላቸው ሕመምተኞች ከድንገተኛ ክፍል ውጪ ሲታዩት 10% (አሥር በመቶ)ቅናሽ ይደረግላቸዋል

<u>የሕክምና ዕዳ መያዣዎች፥</u>
አንድ ታካሚ የአደጋ ወይም የአመጸኝነት ተግባር ሰለባ ከሆነ፣ የመድን ዋስትናቸው
ሌላ ወገን ለጉዳዩ ተጠያቂ እንደሚሆን ከተወሰነ በኋላ አብዛኛውን ግዜ ለሕክምና አገልግሎቶች ክፍያ አያደርግም። በተጨማሪም፣ አንድ ታካሚ የመድን ዋስትና ላይኖረው ይችል ይሆናል፣ ቢሆንም በኃላፊነት ከሚጠየቀው ወገን ካሳ እንዲከፈለው በመጠየቅ ላይ ሊሆን ይችላል። በእነዚህ ሁኔታዎች ላይ፣ ወደፊት ለአካል ጉዳት ካሳ በሚከፈለው ክፍያ ስምምነት ላይ UW Medicine የዕዳ መያዣ እንዲደረግ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል። የዕዳ መያዣ ሲባል፣ ዕዳ መከፈሉን ለማረጋገጥ፣ በአንድ ሰው ቤት-ንብረት ወይም የግል ንብረት ላይ የይገባኛል ጥያቄ ማቅረቢያ መንገድ ነው።

<u>ወደ ሰብሳቢ የተዛወረ ሒሳብ፥</u>
እርምጃዎቹ የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፥
- የክሬዲት ሪፖርት ከመደረጉ በፊት ምላሽ የመስጫ 30 ቀን እንዳላቸው ለዋሶቹ የሚያሳውቅ የመጀመሪያ ማስታወቅያ፥ የክሬዲት ሪፖርት የሚደረገው በ 45ኛው ቀን ላይ ነው።
- የስልክ ጥሪዎች።
- ሕጋዊ ውሳኔን ተከትሎ የደሞዝ ተቀራጭ ማድረግ።
- የሕክምና ዕዳ መያዣዎች።

ወደ ሰብሳቢ የተዛወሩ ሒሳቦችን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ፥
- PFS፣ በማንኛውም ሒሳብ ላይ ለሚወሰዱ ማናቸውም ሕጋዊ እርምጃዎች ፈቃድ መስጠት አለበት።
    - ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ሁነኛ ሥራ ከሌለው፣ PFS ክስ እንዲመሰረት ፈቃድ አይሰጥም።
    - በ UWMC እና በ HMC ስም፣ "ልዩ" ምክትል አቃቤ ሕግ ለኤጀንሲው በሚሰራ ሰው ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወሰዳል።
- በኮንትራት ውስጥ ካሉ ሁለት ኤጀንሲዎች መካከል ካንዱ ጋር ለአንድ ዓመት ተዛውረው የቆዩ ሒሳቦች የሁለተኛ ምደባ ሆኖ በሌላው ኤጀንሲ ውስጥ ይመደባሉ፣ የክፍያ ስምምነቶች ላይ ተደርሶ ከሆነ ወይም ሕጋዊ ፍርድ ተፈርዶ ከሆነ በስተቀር ።
- በቀድሞዎቹ 90 ቀኖች ውስጥ ምንም ድርጊት ካልነበራቸው የሁለተኛ ምድብ ሒሳቦች ከአንድ ተጨማሪ ዓመት በኋላ እንዲመለሱ ይደረጋሉ።
- ከሁለተኛ ምደባ የተመለሱ ሒሳቦች ሊሰበሰቡ እንደማይችሉ ተቆጥረው፣ ከሰብሳቢ ኤጀንሲያችን A/R ይሰረዛሉ።
- ያልተከፈለው ዕዳ በዋሱ የክሬዲት ታሪክ ላይ ለሰባት ዓመት ወይም ደግሞ ሕጋዊ ማስተካከያ ከነበረ ለአስር ዓመት ይቆያል።

<u>በጣም ጥብቅ የሆኑ የዕዳ ስብሰባ እርምጃዎች (ECA)፥</u>
የሚከተሉት እስከሚፈጸሙ ድረስ፣ የታካሚ ሒሳቦች ላይ ማንኛውም የ ECA እርምጃዎች ተፈጻሚ አይሆኑም[1]፣ የ UWMC፣ የ HMC ወይም የተመደቡበት ሰብሳቢ ኤጀንሲ እርምጃ ተፈጻሚ አይሆንምባቸው፥

1. የፋይናንስ እርዳታ ብቁነትን ለመወሰን ተገቢ የሆኑ ጥረቶች እስከሚደረጉ ድረስ።

[1] ECA ዎች የሚያጠቃልሉት፣ በአንድ ግለሰብ ንብረት ላይ የዕዳ መያዣ ማድረግ፣ ግለሰቡን ለክሬዲት ኤጀንሲዎች ሪፖርት ማድረግ፣ ከደሞዙ ተቀራጭ ማስደረግና በሕክምና አስፈላጊ ለሆነ ሕክምና አገልግሎት ከመስጠት በፊት ክፍያ መጠየቅ ወይም ተያዥ ገንዘብ እንዲከፈል መጠየቅ ናቸው።

ተገቢ የሆኑ ጥረቶች ሲባሉ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ[2]፤

a. ለታካሚው፣ ከሕክምና ከመውጣቱ በፊት በግልጽ ቋንቋ የተጻፈ የፋይናንስ እርዳታ አጭር ዝርዝርና ማመልከቻ ይሰጣል እንዲሁም ማመልከቻውን ለመሙላት እርዳታ ይቀርብለታል፤
b. ያልተሟላ ማመልከቻ ከደረሰን፣ ስላልተሟላው መረጃ/ሰነድ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለታካሚው ይላካል፣ ማመልከቻ ወይም ክፍያ በተወሰነ የግዜ ገደብ ውስጥ ክፍያ ካልተከፈለ ማናቸውም ሐኪም ቤቱ (ወይም የሐኪም ወኪል) የጀምረው ወይም የሚቀጥለው የ ECA ዎች ማስታወቂያም ጨምሮ ይላካል፤[3]
c. ሁሉም የቢል መግለጫ ጽሁፎች፣ የፋይናንስ እርዳታን የሚመለከትና ለመረጃ/እርዳታ ለማግኘት የስልክ ቁጥር ያለበትንና የፋይናንስ እርዳታ ሰነድ ኮፒዎች የሚገኙበት የቀጥታ ድረገጽ አድራሻ የተጻፈበት ግልጽ የሆነ ማስታወቂያን ይዘዋል፤
d. የተሟሉ የፋይናንስ እርዳታ ማመልከቻዎች በተገቢው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈጻሚ ሆነው ለታካሚው ስለ ውሳኔው በጽሑፍ ማስታወቂያ ይደርሰዋል፣ ቀሪ ዕዳ ካለ ደግሞ ወቅታዊ የቢል ስቴትመንት ይሰጠዋል፣ እንዲሁም በማመልከቻ የተደገፈ በተፈቀደው የግዜ ገደብ ውስጥ ክፍያ ተከፍሎ ከነበረ፣ ገንዘቡ ይመለስለታል።
e. ሐኪም ቤቶች፣ ታካሚው ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሚሆኑ በገቢ አቅም ለተመደቡ የመንግስት እርዳታ ፕሮግራሞች ብቁነት በመሠረተው መረጃ መሰረት፣ ሊገኝ ስለሚችል በጣም ለጋስ የፋይናንስ እርዳታ ታካሚው ብቁ ለመሆኑ ውሳኔ በማድረግ የተገቢ ጥረቶች መስፈርትን ሊያሟሉ ይችላሉ።
f. ሐኪም ቤቱ፣ በፋይናንስ እርዳታ ማመልከቻ ላይ የተጠየቀውን መረጃ/ሰነድ ሙሉ በሙሉ ላላሟላ ታካሚ የፋይናንስ እርዳታ ለመስጠት ሊመርጥ ይችላል።

2. ከሐኪም ቤት ከወጣ በኋላ የመጀመሪያው የቢል መግለጫ ከተላከበት ቀን ጀምሮ 120 ቀኖች ካለፉ፤ እና

3. የሚከተሉት የማሳወቂያ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ (የ ECA ከመጀመሩ ቢያንስ ከ 30 ቀኖች በፊት)፦
   a. የፋይናንስ እርዳታ መኖሩን የሚገልጽ በጽሑፍ የተዘጋጀ ማስታወቅያ ተልኳል፤
   b. በግልጽ ቋንቋ የተጻፈ የፋይናንስ እርዳታ መግለጫ አጭር ዝርዝር አንቀጽ፤
   c. ክፍያ አለመከፈሉ ከተገለጸ በኋላ ለሚደረግ እርምጃ(ዎች) ማስታወቅያ ከተሰጠ፤
   d. ክፍያ ካልደረሰ፣ ከየትኛው ቀን ጀምሮ እርምጃ(ዎች) እንደሚወሰድ(ዱ) የሚያሳስብ ማስታወቅያ፣ እና
   e. ስለ ፋይናንስ እርዳታ ፖሊሲና ማመልከቻ ከታካሚው ጋራ የቃል ውይይት ለማድረግ ሙከራዎች ተደርገዋል።

4. ከሐኪም ቤት ወጥተው የመጀመሪያው ቢል ከተላከበት ከ 150 ቀኖች በኋላ ስለ ክሬዲት ሪፖርት ማድረግ ይጀመራል።

5. ሳይከፈል ግዜ ላለፈበት ቢል፣ ከሐኪም ቤት ከወጣ የመጀመሪያው ቢል መግለጫ ከተላከበት ከ 240 ቀኖች በፊት ክስ ላይመሰረት ይችላል።

6. ታካሚው ለፋይናንስ እርዳታ ብቁ መሆኑን ለመወሰን በቂ ጥረት ተደርጓል።

---

[2] ሐኪም ቤት፣ ከታካሚ የፈቃድ መስጫ ፎርማ በማግኘቱ ብቻ፣ የታካሚውን ብቁነት ለመወሰን ተገቢ የሆነ ጥረት ለማድረግ ሳይችል፣ ወይም ለእርዳታ ብቁ አለመሆንን አስተማማኝ ወይም ስህተት በሆነ መረጃ ወይም ከታካሚው መረጃው የተገኘው በማስጨነቅ ወይም በማስፈራራት መሆኑን የሚያሳምን ምክንያት ኖሮት ሐኪም ቤቱ ውሳኔውን ያደረገ ከሆነ፣ ሐኪም ቤቱ ተገቢውን ጥረት እንዳላደረገ ነው።

[3] በ ECAዎች የተጀመሩ ማናቸውም ነገሮች እንዲቆሙ ይደረጋሉ።

ሁሉንም ታካሚዎች/ዋሶች እኩል ማስተናገድ፥

UWMC እና HMC፣ በዚህ የታካሚ ሒሳቦች መሰብሰቢያ ፖሊሲ መሠረት ያስፈጽማሉ። በምንም ዓይነት ሁኔታ፣ ይህ ፖሊሲ በተግባር ላይ በሚውልበት ወቅት ዕድሜ፣ ዘር፣ የቆዳ ቀለም፣ ሀይማኖት፣ ጾታ፣ ጾታዊ ዝንባሌ ወይም የትውልድ ሀገር በግምት ውስጥ አይገቡም።

የዚህ ፖሊሲ ግልባጭ፣ እንዲሁም ደግሞ የፋይናንስ እርዳታ ፖሊሲ፣ በግልጽ ቋንቋ የተጻፈ የፋይናንስ እርዳታ አጭር ዝርዝር እንዲሁም የፋይናንስ እርዳታ ማመልከቻ ግልባጮችን የሚከተሉትን በማነጋገር ማግኘት ይቻላል፥

Harborview Medical Center (HMC)
Financial Counseling
325 9th Ave; Mail Stop 359758
Seattle, WA 98104-2499
206.744.3084
ከሰኞ-ዓርብ ከጠዋት 8:00 – 4:30 ከሰዓት

UW Medical Center (UWMC)
Financial Counseling
1959 NE Pacific Street, Mail Stop 356142
Seattle, WA 98195-6142
206.598.3806
ከሰኞ-ዓርብ ከጠዋት 8:00 – 4:30 ከሰዓት

HMC & UWMC
Patient Financial Services
P.O. Box 95459
Seattle, WA 98145-2459
206.598.1950 ወይም 1.877.780.1121
ፋክስ 206.598.2360
ከሰኞ-ዓርብ ጠዋት ከ8:00 – 4:30 ከሰዓት

ድረ ገጽ፥ http://www.uwmedicine.org/financialassistance